# አምላክ ለጸሎቱ መልስ ሰጥቶታል

***መመሪያ፦*** ይህን መልመጃ ጸጥታ በሰፈነበት ቦታ ሆነህ ሥራ። ጥቅሶቹን ስታነብ በቦታው እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች ሲነጋገሩ ድምፃቸውን ለመስማትና ስሜታቸውን ለመረዳት ሞክር። ታሪኩ ሕያው እንዲሆንልህ አድርግ።

***ዋነኞቹ ባለታሪኮች፦*** ነህምያ፣ ንጉሥ አርጤክስስ፣ ሰንባላጥ እና ጦብያ

***ታሪኩ በአጭሩ፦*** ነህምያ ወደ አምላክ ጸለየ፤ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንዲፈቅድለት ንጉሡን ጠየቀው፤ ነህምያ የተለያዩ እንቅፋቶችን ተወጣቷል።

## 1 ሁኔታውን ለማስተዋል ሞክር።—ነህምያ 2:1-20ን አንብብ።

ከታች የተጠቀሱት ባለታሪኮች ምን እንደሚመስሉ ለመግለጽ ሞክር።

ነህምያ፦ ____________________

ንጉሥ አርጤክስስ፦ ____________________

ሰንባላጥ እና ጦብያ፦ ____________________

ነህምያ ያቀረበው ጸሎት አጭር የነበረው ለምን ይመስልሃል? ____________________

____________________

ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ በከተማይቱ የነበረው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመግለጽ ሞክር። (*ቁጥር 13ን እና 14ን እንደገና አንብብ።*)

____________________

ነህምያ በቁጥር 17 ላይ ያለውን ሐሳብ ሲናገር ምን ዓይነት የድምፅ ቃና የነበረው ይመስልሃል?

____________________

## 2 ጥልቅ ምርምር አድርግ።

ነህምያ ስለ ምን ጉዳይ የጸለየ ይመስልሃል? (*ነህምያ* 1:4-11ን *አንብብ።*)

____________________

ነህምያ፣ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ አርጤክስስ እንደሚፈቅድለት እርግጠኛ የነበረው ለምን ይመስልሃል? (ዕዝራ 7:1-6ን እና ምሳሌ 21:1ን አንብብ።)

____________________

አይሁዳውያን 'እጃቸውን ለበጎ ሥራ ያበረቱት' እንዴት ነው? (*ነህምያ* 2:18ን *በ1954 ትርጉም* እና ኢሳይያስ 35:3ን *አንብብ።*)

____________________

ነህምያ ለሰንባላጥና ለጦብያ ከሰጠው ምላሽ ይበልጥ የነካህ ምንድን ነው? (*ነህምያ* 2:20ን *አንብብ።*)

____________________



www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

3

## ከዚህ ታሪክ ያገኘኸውን ትምህርት ተግባራዊ አድርግ።

ከዚህ በታች ስለሰፈሩት ሐሳቦች ምን ትምህርት እንዳገኘህ ጻፍ፦

ጸሎት ስላለው ኃይል ______________________________

______________________________

ይሖዋ፣ አገልጋዮቹ በድፍረት እንዲናገሩ የሚረዳቸው እንዴት እንደሆነ ______________________________

______________________________

4

## ራስህን ጠይቅ፦

የሚያበሳጭ ወይም የሚያሳዝን ነገር ሲያጋጥመኝ የነህምያን ምሳሌ መከተል የምችለው እንዴት ነው?

______________________________

______________________________

ሌሎች በእምነቴ ምክንያት ሲቃወሙኝ በይሖዋ እንደምታመን ማሳየት የምችለው እንዴት ነው?

______________________________

______________________________

ከዚህ ታሪክ የማገኘው ለእኔ በጣም አስፈላጊ የሆነው ትምህርት የትኛው ነው? ለምን?

______________________________

______________________________

______________________________

**ተጨማሪ ሐሳብ፦** ምርምር ማድረግ የምትችልባቸውን መሣሪያዎች በመጠቀም የጥንቶቹን የሱሳ እና የኢየሩሳሌም ከተሞች በካርታ ላይ ፈልግ። (ነህምያ 1:1) በእነዚህ ከተሞች መካከል ያለውን ርቀት አስላ፤ ከዚያም ዘመናዊ የመጓጓዣ ዘዴ ሳትጠቀም እንደ ነህምያ ከቤትህ ይህን ያህል ርቀት መጓዝ ምን ያህል ከባድ እንደሚሆን ለማሰብ ሞክር።



JW.ORG™

ይህን ፒዲኤፍ ከwww.jw.org/am ላይ አውርደህ ማተም ትችላለህ



www.jw.org/am © 2013 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania